# ሱዳን የኢትዮጵያን መሬቶች በሃይል ተቆጣጠረች።

*May 4, 2008*

- 1600 ኪሎ ሜትር ድንበር ተጥሷል፤ ሁመራ መተማ ቋራ አሶሳን ይጠቀልላል
- ኢትዮጵያውያንን አስራ ወሰደች የተረፉትም ተፈናቅለዋል
- ከፍተኛ ንብረት ተዘርፏል የተረፈውንም አቃጥለዋል
- የመለስ ዜናዊ መንግስት ድንበሩንም ሕዝቡንም ለወራሪው ***የድርቡሽ*** ጦር አሳልፎ ሰጠ

<u>በወራሪው የሱዳን/ድርቡሽ ጦር በእስር የተወሰዱ ከፊል ኢትዮጵያውያን ስምዝርዝር</u>

1. ወርቁ ሽፈራው
2. ማሩ ትኩየ
3. ምስጋናው ሙሉ
4. ገብሬ አዳነ
5. ደረጀ አለሙ
6. ምጥን ዳኘ አለሙ (ሴት)
7. አብዲ አይደል
8. አራጋው
9. ማህሪ መብራቱ
10. ኢብራሂም
11. መለሰ ረዳ
12. አሊ አብዲ
13. እንድሪስ

ስማቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ኢትዮጵያውያንና ሌሎች ከሰላሳ ያላነሱ ስማቸውን ለይተን ማዎቅ ያልቻልናቸው ወገኖች ሱዳን ውስጥ "**የሱዳን ግዛት ውስጥ በህገውጥ መልክ በመስፈር ወንጀል**" ፍርድ ቤት ተከሰው እያንዳንዳቸው ወደ መቶ ሽህ ዶላር መቀጮ እየተጠየቁ መሆኑን ከአካባቢው ያገኘናቸው የዜና ምንጮች አስረድተዋል። ታሳሪዎቹ ከኢትዮጵያ መንግስት ህጋዊ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው የ 15 አመት ሊዝ ተፈራርመው ከሚንቀሳቀሱ ባለሃብቶች ተቀጥረው የሚሰሩ እንደነበሩ ለማዎቅ ተችሏል። የእርሻ ቦታዎቹ ባለቤትነትም በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት ደግሞ አሜሪካዊ እና እስራኤላዊ የሆኑ ባለሃብቶች እንደሚገኙበት

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ታውቋል። አንዱ ባለሃብት ብቻ ወደ ሶስት ሚሊዮን ብር የሚገመት ንብረት በወራሪው የሱዳን ጦር እንደተዘርፈበትና እንደወደመበት በምሬት ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም የሱዳን ወታደሮች ያሰሯቸውንም ሆነ በስደት ላይ ያሉ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን ጭምር አሁን በሃይል የተቆጣጠሯቸው የኢትዮጵያ መሬቶች የሱዳን መሆናቸውን እናምናለን በማለት እንዲፈርሙ እያስገደዷችው እንደሆነ ከቦታው ከመጡ ተፈናቃዮች ማጣራት ችለናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያውያን ዋና መነጋገሪያ የሆነው ግልጽ የሱዳን ወረራ ሊፈጸም የቻለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መሬቶቹን በድርድር አሳልፎ ስለሰጠ መሆኑ በግልጽ እየተነገረ ነው። እንደሚታወቀው ላለፉት አስር አመት የሚሆን ጊዜ ***የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ኮሚሽን*** የሚል አካል ተቋቁሞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ይሄው አካል ሱዳንን ያካልላሉ የተባሉ በአሁኑ አጠራር የትግራይ የአማራ የቤንሻንጉልንና የደቡብ ክልል የስርአቱ ተወካዮችን ያቀፈ ሲሆን በሱዳንም በኩል ተመሳሳይ አወቃቀር አለው። ኮሚሽኑ ያደርጋቸው የነበሩት የአስር አመታት እንቅስቃሴ በመንግስት ሚዲያ በተደጋጋሚ ይነገር የነበረው የሁለቱ አገሮች የመሰረተ ልማትና የንግድ ልውውጥ በሚል ጥቅል ሽፋን ቢሆንም መደምደሚያው ግን 1600 የሚዘልቅን ሉአላዊ የኢትዮጵያን ግዛት አሳልፎ ለሱዳን መስጠት ሆኗል።

ከጅምሩ አካሄዱ ያሰጋቸው ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ከአራት አመት በፊት <u>**የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ኮሚቴ**</u> የሚል አካል አቋቁመው ወቅታዊ መረጃዎችን ለሕዝብ ሲያዳርሱ ከመቆየታቸውም በላይ ለክልልና ለፌደራል የኢትዮጵያ ባለስልጣናት መልስ ያልተሰጠው ተደጋጋሚ አቤቱታና ማብራሪያ እንደቀረበ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ኮሚቴ ስራውን በተጠናከረ ለመቀጠል እንዲያስችለው በተለያየ የሙያ ዘርፍ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ሞያተኞችን በህግ፤ በታሪክ፤ በሚዲያና ቅስቀሳ የስራ ክፍሎች በስሩ አቅፎ ስራውን እንደቀጠለ ለማወቅ ተችሏል።

በግፍ በወራሪው የሱዳን/ድርቡሽ ጦር የተፈናቀሉ በሽዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ለዝንተ አለም የኖሩበትን መሬት ለማስጠበቅ እልህ አስጨራሽ ትንቅንቅ እያደረጉ መሆናቸውን ማዎቅ ተችሏል። አቅማቸው ያልፈቀደ ብዙዎችም ተፈናቅለቅ ወደ ጎንደር ከተማ እየሰፈሩ ይገኛሉ። ይህን ሪፖርት ስናጠናክርም የጥቃቱ ሰለባዎችን በስልክ ማናገር ችለናል። ተፈናቃዮችም ለመንግስት እንኳን አቤት የማንልበት ዘማን ደረሰን በማለት በቁጭት ይናገራሉ። ስለሆነም የድረሱልን ጥሪያችንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አድርሱልን በማለት ያደራ መልእት አስተላልፈዋል።

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ መንበሩን በሃይል ከተቆጣጠረ አስራ ሰባት አመት ሲሆነው፤ የኢትዮጵያም ሉአላዊነት መደፈር ያን ያህል መንገድ ተጉዟል። የኤርትራ ጥያቄ፤ የአሰብ ጉዳይ፤ አሁን ደግሞ ለሱዳን የኢትዮጵያን ግዛቶች አሳልፎ ሰጥቶም በስልጣን ላይ ተደላድሎ መቆየቱ ዋናው መንስኤ "ኢትዮጵያውያኖች የመለስ ዜናዊን መሰሪ የባእድ አገዛዝ በቅጡ አለመረዳታችን ነው" ሲል የኢትዮሚዲያ ዋና አዘጋጅ የሆነው አቶ አብርሃ በላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ላነሳሁለት ጥያቄ የተለመደ አስተያየቱን ገልጿል።

ኢትዮሚዲያ ይሄንን አይን ያወጣ ያገር ሉአላዊነት መደፈርን እያወገዘ ሆሉም ኢትዮጵያዊ ያገሩን ድንበር ለማስጠብቅ ታሪካዊ ሃላፊነቱን እንዲወጣ ማስታወስ እንወዳለን። ካሁን በፊት እንዳደረግነው ሁሉ ጉዳዮን በቅርበት እየተከታተልን ለሕዝብ እናቀርባለን።

**የኢትዮሚዲያ ሪፖርተር**

**ሙሉነህ ዮሃንስ** muluneh@ethiomedia.com

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com